## የግል አስተያየት

## አንጃዉም ተገነጠለ፤ መድኅንም ነፃ ወጣ!

### ከኦክቶበር 19 እስከ አፕሪል 19

ከሸዋይልማ ኪዳኔ /ጀርመን/

እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 19.ቀን 2002 ዓ.ም ከተካሄደው ጠቅላላ የመድኅን ጉባዔ ወዲህ በመድኅን ውስጥ የተፈጠረው መከፋፈል የብዙውን ኢትዮጵያዊ ትኩረት ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሳበና የድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎች እስከ አፕሪል 19 ቀን 2003 ዓ.ም ሲያወያይና በጣሙን ሲያሳዝን የቆየ ጉዳይ ነው። ከዚያ ወዲህ ግን እንደማንኛውም ክስተት ጊዜውን ጨርሶ አልፏል። እኔም በመድኅን ውስጥ ስለተፈጠረው ክፍፍል ለመጻፍ ያስገደዱኝ ሁለት ምክንያቶች አሉኝ። አንደኛው እኔ በግሌ እንደማንኛውም የመድኅን አባል ጉዳዩን ከሥር ከመሠረቱ የተከታተልኩ በመሆኔ በዚህ ጉዳይ ላይ የግል አስተያየቴን ሳልሰጥ ማለፍን ሕሊናዬ ስለአልፈቀደልኝ ስለተፈጠረው ክፍፍል ወይም አለመግባባት የበኩሌን ግንዛቤ ለአንባቢያን ማካፈል ፈለግሁ። ሁለተኛው በስሙ ፖለቲካ የሚካሄድበትና የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመድኅን ውስጥ ስለተፈጠረው ክፍፍል የማወቅ መብት እንዳለው አጠያያቂ አይደለም። በዚህ በኩል በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የተለያዩ የሬዲዮ ጣቢያዎች ከመድኅን ሊቀመንበር ፕ/ር ሥዩም ገላዬ ጋርና እንዲሁም በድርጅቱ ውስጥ አንጃ ከፈጠሩት ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ ጋር ያደረጓቸው ቃለ ምልልሶች፣ በተጨማሪም መድኅን በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ጠርቶ ባካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የፓርቲው ሊቀመንበር ፕ/ር ስዩም ገላዬ ሊትዮጵያውያን በድርጅቱ ውስጥ ስለተፈጠረው አለመግባባት በቂ የሆነ ሥዕል እንዲያገኙ ያደረጉ በመሆኑ በሰሜን አሜሪካ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ በጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዳገኘ ሙሉ እምነት አለኝ። እንግዲህ ወደ ዋናው ቁምነገር እንመለስና በመድኅን ውስጥ የተፈጠረው መከፋፈል እንዴትና መቼ ተጀመረ? ለመከፋፈል ምክንያት ሆኖ የቀረበው ሐሳብ ምንድን ነው? የመድኅን 6ኛ ጠ/ጉባዔ መቼ ተካሄደ? የቅርንጫፎች የስብሰብ ጥሪ ምክንያት ምን ነበር? በጉባዔው ላይ እንዲገኙ የተላኩ የየቅርንጫፍ ተወካዮች (ለምሳሌ የጀርመን ቅርንጫፍ) ተወካዮች ሪፖርት ምን ይመስል ነበር? የመድኅን 6ኛው ቀጣይ ጉባዔ የሚባል ነገር ከየት መጣ? የቀጣዩ ጉባዔ ውጤት ምን ሆነ? ኮ/ል ጎሹ ከመድኅን ለምን ተባረሩ? ... ሌሎችንም ብዙ ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል። ሆኖም ግን ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠትና ለማብራራት በማደርገው ጥረት ውስጥ ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ነጥቦች እያነሳሁ መልስ በመስጠት በፓርቲው ውስጥ ስለተፈጠረው መከፋፈል የግል አስተያየቴን አቀርባለሁ።

## የመድኅን ጠቅላላ ጉባዔ

የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) 6ኛው ጠቅላላ ጉባዔ በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 19 ቀን 2002 ዓ.ም ተካሄዷል። በጉባዔው ላይ የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተው ውይይት ተካሂዶባቸዋል። ይሁን እንጂ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት አብዛኛውን የጉባዔውን ሰዓት የወሰደው በጉባዔው ቀደም ተብሎ ያልተያዘውና በአቶ አልአዛር ዋካ ለቤቱ የቀረበው አጀንዳ ነበር። ሐሳቡ አቶ አልአዛር ለጉባዔው እንዲያቀርቡ የተሰጣቸው የቤት ሥራ እንጂ የሐሳቡ አፍላቂና ባለቤት ሆነው አይደለም። የሐሳቡ ዋና ይዘት ወደ ሀገር ቤት (ኢትዮጵያ) እንግባና ትግሉን በሰላማዊ መንገድ እናካሂድ የሚል ነው። ከዚህ ተናጋሪ ቀጥሎ የሐሳቡ ባለቤት የሆኑት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከተቀመጡበት ተነስተው እቤታቸው በእጃቸው ጽፈው በፎቶ ኮፒ ያባዙትን አንድ ገጽ ከግማሽ የሆነ ጽሑፍ ለጉባዔው ተሳታፊ ማደል ጀመሩ። የጽሑፉ ርእስ "የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) ጠቅላላ ጉባዔ 6ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ" ይላል። ጽሑፉ በሁለት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ አሳልፏል። የመጀመሪያው በመድኅን የመተዳደሪያ ድንብ አንቀጽ 9.4 ላይ የሰፈረው ተሻሽሎ መድኅን አምባገነኑን የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ በሰላማዊ መንገድ እንዲያስወግድ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መድኅን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባና ትግሉን በይፋ እንዲያካሂድ የመድኅን ጠቅላላ ጉባዔ 6ኛ መደበኛ ስብሰባ ውስኗል ይላል። በመቀጠልም ኮ/ል ጎሹ የትግል ሥልት ለውጥ እንደሚያስፈልግ በማብራራት በመለወጥ ላይ የሚገኘውን ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሁኔታና የኃይል አሰላለፍ በተለይም ከሰፕቴምበር 11 በኋላ የተፈጠረውን ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ይዘትና ዝንባሌ በተመለከ ለጉባዔው ተሳታፊ በሰፊው አስረዱ። ቀጥሎም አቶ ቾኑ ተረፈ የቀረበውን ሐሳብ እንደ አቶ አልአዛር ዋካ አስቀደመው የሚያውቁትና የዚሁ ቡድን ጠንሳሽ እንደመሆናቸው ሐሳቡን በመደገፍ ያጠናክራሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የቀረበውን ሐሳብ አስቀድመው ከሚያውቁ ከአምስት የማይበልጡ አባላት በስተቀር ብዙሃኑ

የጉባዔው ተሰታፊ ለሐሳቡ ፈጽም ባዕድና እንግዳ ነበር። በሌላ በኩል እንደዚሁ አንዳንድ አባላት ሀሳቡን በመቃወም ምክንያታቸውን ገለጹ። ጉባዔው በኮሎኔል ጎሹ የቀረበው ሐሳብ በዕለቱ ተወያይቶበት ውሳኔ ለማሳለፍ የማይቻል መሆኑን በማመን፣ በመላው ዓለም የሚገኙ የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ጥልቅ ውይይትና ጥናት አድርገውበት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውጤቱን ለጠቅላላ ጉባዔው እንዲያሳውቁ ወስኖ ይህንንም የሚያስፈጽም አምስት አባላት ያሉበት በፕ/ር አቻምየለህ ደበላ የሚመራ ኮሚቴ አቋቋመ። በመቀጠልም ጉባዔው የቀረቡለትን  እጩዎች ካሁን በፊት ይጠቀምበት በነበረው የምርጫ ባሕል መሠረት ፓርቲውን ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የሚመራ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ይመርጣል። ም/ሊቀመንበሩ ዙሩን(ተርሙን) የፈጸመ በመሆኑ በመትኩ ከጀርመን አንድ አዲስ ም/ሊቀመንበር ተመርጦ ጉባዔው ተጠናቀቀ። ጉባዔው ተካሂዶ በኮ/ል ጎሹ ወልዴ ለቀረበው ሐስብ አንድ ኮሚቴ ማቋቋሙንና ምርጫ ማካሄዱን በኦክቶበር 30 ቀን 2002 ዓ.ም ፓርቲው ያወጣውን መግለጫ መመልከት ይቻላል።

በእኔ እምነት ጉባዔው አንድ ድርጅታዊ ተግባር ሳይፈጽም አልፏል። ይኸውም ጉባዔ እየተካሄደ በመሐል ተንስቶ በአጀንዳ ያልተያዘ አዲስ ሐሳብ ማቅረብና የስብሰባውን መንፈስ ለመቀየር መሞከር አግባብ አይደለም። ካስፈለገም አጀንዳው ጸድቆ ወደ ውይይት ከመገባቱ በፊት ማቅረብና ቤቱን ማስፈቀድ ያስፈልግ ነበር። በእለቱ የተፈጸመው ግን ከዚህ መንፈስ የራቀና አፍራሽ ተልዕኮ ያለው የሚመስል ነበር። በኮ/ል ጎሹ ተዘጋጅቶ "የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ" ተብሎ የተበተነው ጽሑፍ በራሱ ምን ያህል የግል እምነትን በፓርቲው ላይ ለመጫን የተደረገ ሙከራ እንደነበርና በዲሞክራሲያዊ አሠራር ተቀባይነት የሌለው ንቀት የተሞላበት፣ ከሁሉም በላይ የፓርቲውን ድንብና ሥርዓት የጣሰ ተግባር በመሆኑ ምንም እንኳን ኮ/ል ጎሹ ለፓርቲው ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስግባት የዲሲፕሊን እርምጃ ባይወሰድም ተግባራቸው ተውግዞ አስፈላጊው ምክርና ተግሳጽ መሰጠት ነበረበት። ያለመታደል ሆኖ ይሉኝታ የሚሉት ጎታች ኢትዮጵያዊ በሽታ የጉባዔዉን ተሳታፊ አፍ በመለጎም ይህን የማንአለብኝነት ተግባር በዝምታ ሊታለፍ ችሏል። ሌላ ማየት ያልቻልነው ቁም ነገር ድግሞ ኮ/ል ጎሹ ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ የወሰኑ መሆናቸው በግልጽ ቋንቋ ባቀረቡት የውሳኔ ሐሳብ ላይ ሠፍሮ እያለ ስለጉዳዩ አስቀድሞ ወስኖ ከመጣ ሰው ጋር ያን ያህል ጊዜ ማጥፋት የጉባዔውን ተሳታፊዎች ሆደ ሰፊነት ከማሳየቱም በላይ በቤቱ ውስጥ ምን ያህል ቅንነት እንደነበርም ያስረዳል። ኮ/ል ጎሹ ከፓርቲው የተለዩት  አዘጋጅተው ቤቱ እንዲያጸድቅላቸው ያቀረቡትን ሀሳብ ጉባዔው አባላት ተወያይተውበት አስተያየት ከሰጡበት በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲወሰን ሲስማማ ነው። ከዚህ ጉባዔ በኋላ በአንጃው በኩል የቴሌፎን ፖለቲካ ሥራዬ ተብሎ ተያዘ። ከቅርንጫፍ የአመራር አባላት ጀመሮ እስከ ተራ አባላትና ደጋፊዎች ድረስ እንደ አመቺነቱ በቴሌፎን፣ በደብዳቤና በአካል ተገኝቶ በማነጋገር በፓርቲው ጠንካራ የአመራር አካላት ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል የማጥላላት ዘመቻ ተከፈተ። ይሁን እንጅ ከጥቂት የዋህ አባላት በስተቀር የዚህ አፍራሽ ተልዕኮ ሰለባ ሊሆንላቸው የሚችል አልተገኘም። በአንጻሩም ከአባላት የሚያገኙት መልስ ለምን ድንብ ትጥሳላችሁ? ሥርዓትን በተከተለ መልኩ ቅረቡና እንወያይ የሚል ነበር።

## የመድኅን ቅርንጫፎች

የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቡድን ሐሳቡን ወደ ጉባዔው ከማቅረቡ በፊት አንዳንድ ዝግጅቶችን ማድረጉን የሚያሳይ በቂ ምልክቶች አሉ። በዚህ አጋጣሚ ዕድሜ ለደርግ መንግሥት በሚገባ አስተምሮን ያለፈውንና አሁንም በሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የሚጠቀምበትን ድርጅታዊ የሚሉትን አሠራር እንድናስታውስ ያደርገናል። ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ በስብሰባ ላይ ለተሳታፊዎች ይቀርብና ከሌላ ወገን ሰምታችሁ እንዳትደነግጡ አቀረብንላችሁ እንጅ እናንተ እንድትወያዩበትና ውሳኔ እንድትሰጡበት አይድለም ያቀረብነው እያሉ ነው በድፍረት የወያኔ ባልሥልጣኖች በየስብሰባው የሚናገሩት። ኮ/ል ጎሹ ይህን በመድኅን ስም እንዲያልፍ የሚፈልጉትን ውሳኔ ቤታቸው አዘጋጅተው ሲመጡ አስቀድመው በጉባዔው ላይ ተነስቶ ሐሳብ የሚያቀርብ አባል፣ ቀጥሎም ድጋፉን የሚገልጽ፣ ከዚያ ራሳቸው ተንስተው ያዘጋጁትን ጽሑፍ ለጉባዔው ተሳታፊ ሲያድሉና የዓለምን ውቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታና የኃይል አሰላለፍ በማብራራት የትግል ሥልት ለውጥን አስፈላጊነት የግል ትንታኔ ሲያቀርቡ የሌላውን ልብ በቀላሉ የሚያገኙና የዚያኑ ዕለት እሳቸውና ቡድናቸው በሚፈልጉት መልክ የሚወሰን መስሏቸው እንደመጡ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። እዚህ ላይ ኮ/ሉ የፓርቲውን አባላት የፖለቲካ ንቃትና ግንዛቤ ግምትም ውስጥ ያስገቡት አይመስልም፡፡

ሌላው የኮ/ል ቡድን በቂ ዝግጅት የማድረጉ ምልክት የሚሆነን እዚያው ሴራው እሚካሄድበት ሰሜን አሜሪካ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ቅርንጫፎች በአጭር ጊዜ ውስጥ በአባላት ስም በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የቀረበውን የትግል ሥልት ለውጥ ደግፈው ውሳኔ ማሳለፍ ነው። ከደጋፊዎቹ ውስጥ ለምሳሌ በ10.11.2002 የሎሳንጀለስ ቅርንጫፍ በሊቀመንበሩ በአቶ አሸናፊ ለማ ተፈርሞ የቅርንጫፉን ማሕተም የያዘ መግልጫ የኮ/ል ጎሹን ሐሳብ በመደገፍና የ6ኛውን ጠ/ጉባዔ ምርጫ በደንቡ መሰረት አልተካሄደም በሚል ተበትኗል። በጣም የሚገርመው ግን ራሳቸው አቶ አሸናፊ የ6ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በአካል በመገኘት ጉባኤው የቀረበውን ሐሳብ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ኮሚቴው አስጠንቶና አወያይቶ እንዲያቀርብ ሲወስን ምንም ተቃውሞ ያላሰሙና እንዲያውም የዚሁ አጥኚ ኮሚቴ አባል በመሆን ከተመረጡት አንዱ ናቸው። እኔ ለአቶ አሸናፊ

ያለኝ አንድ ጥያቄ ቢኖር ለምን በጉባዔው ዕለት ከምርጫው በኋላ ተነስተው የዶ/ር ሥዩም ገላዬን በድጋሚ በሊቀመንበርነት መመረጥ ደግፈው ከማጨብጨብ ይልቅ ምርጫው በደንቡ መሠረት አልተካሄደም ብለው አልተቃወሙም ? በኮሚቴው አባልነት ሲመረጡስ ለምን ተቃውሞ አላቀረቡም? በጣም የሚያሳዝነው ሎስአንጀለስ ከተመለሱ በኋላ በቅርንጫፉ ስም ከአንጃው የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ለመወጣት ሲሉ ብቻ የትግል ስልት ለውጡን እንደሚደግፉና ምርጫውን እንደሚቃወሙ መግለጫ ማውጣታቸው ነው። በመቀጥልም አቶ ሞገስ ኃ/ጊዮርጊስ የሚመሩት የዋሽንግተንና አካባቢው ቀጠና "የትግል ሥልቱ በሰላማዊ መንገድ" እንዲሆን ውሳኔ አስተላላፈ። ጉባዔም እንድገና እንዲጠራ ጠየቀ። አንጃው የራሱ መግለጫዎች እንደ ገደል ማሚቶ እያስተጋቡ በሚያሰሙት ድምፅ ራሱን በአንድ ሰሞን የደስታ ፖለቲካ አሰከረ። በሌላ በኩልም እንደዚሁ የጀርመን፣ የካናዳ፣ የዋሽንግተን፣ የኒዮርክ ... ወዘተ ቅርንጫፎች የፓርቲው ደንብና የ6ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ዉሳኔ እንዲከበር በመጠየቅና የፓርቲውን አመራር በመደገፍ የአቋም መግለጫ አወጡ፤፤ ውሳኔዎችንም አሳለፉ፤፤ የፓርቲው መተዳደሪያ ድንብ በሚያዘው መሠረት ቅርንጫፎች ጉባዔ እንዲጠራ መጠየቅ ይችላሉ። ለዚሁም የድርጅቱ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ጉዳዩን ካመነበትና ስብሰባው እንዲጠራ የሚፈልጉት ቅርንጫፎች ቁጥር ሁለት ሦስተኛ ከሆነ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። እዚህ ላይ ግን መታወቅ ያለበት ቁምነገር ቢኖር ቅርንጫፎቹ ስብሰባ እንዲጠራ የጠየቁበት ጉዳይ አዲስ ያልሆነና በመድኅን 6ኛ ጠ/ጉባዔ ላይ ቀርቦ አባላት እንዲወያዩበት ስምምነት ላይ የተደረሰበት በመሆኑ የፓርቲውን ከፍተኛ አካል የሆነውን የጠቅላላውን ጉባዔ ውሳኔ ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ የትግል ሥልትን አስመልክቶ በቅርንጫፍ ደረጃ ውሳኔ ማስተላለፍ ፈጽሞ ሕገ ወጥና የድርጅቱን ድንብ የሚጥስ በመሆኑ የዲሲፒሊን እርምጃ እስክ መውሰድ የሚያደርስ ተግባር ነው። ቅርንጫፎች የድርጅቱን ፖሊሲ፣ ደንብና ፕሮግራም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ማስተላለፍ ፈጽሞ አይችሉም። የመወሰን ሥልጣን ያለው የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካል የሆነው ጠቅላላ ጉባዔው ብቻ ነው። ይህ ማለት ግን ቅርንጫፎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አቋም መግለጽ አይችሉም ማለት አይደለም።

በአባልነት የምገኝበት የጀርመን ቅርንጫፍ በመድኅን 6ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ እንዲገኙ ሁለት የቅርንጫፍ የሥ/አስኪያጅ ኮሚቴ አባላትን የላክ ሲሆን እንድሁም በተጨማሪ አቶ ማሞ ይሁኔ በጊዜው የፓርቲው የሥራ አመራር አባል በመሆናቸው እርሳቸውን ጨምሮ ከጀርመን የመድኅን ቅርንጫፍ ሦስት አባላት በጉባዔው ላይ ተገኝተዋል። ጉባዔው ከተካሄደ በኋላ ሁለቱ የቅርንጫፉ የሥራ አሥፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ባቀረቡት ሪፖርት በጉባዔው ላይ የኮ/ል ጎሹ ሐሳብ ለቤቱ ቀርቦ ከላይ በጠቀስኩት መልኩ ውይይት ተካሂዶበት አንድ የጥናት ኮሚቴ እንደተቋቋመና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሚጠራው ጠ/ጉባዔ ውሳኔ እንዲሰጥበት የተውሰነ መሆኑን ጠቅሰው፣ አቶ ማሞ ይሁኔ በም/ሊቀመንበርነት የሚያገለግሉበትን የሥራ ዘመን (ተርም) የጨረሱ በመሆናቸው በምትካቸው ከጀርመን ሥ/አ/ኮሚቴ ውስጥ አንድ አባል በመተካት ጉባዔው የሚጠበቅበትን ተግባር አጠናቅቆ መነሳቱን ገልጸዋል። እንደዚሁም አቶ ማሞ ይሁኔ ራሳቸው በአባልነት በሚገኙበት የደቡብ ሄሰን ን/ቅርንጫፍ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ባቀረቡት ሪፖርት ጉባዔው የተጠበቀበትን ተግባር በሚገባ ማከናወኑን አስረድተዋል። ይህም በቃለ ጉባዔ የተያዘ በመሆኑ ማንም ማየትና ማረጋገጥ ይችላል። እንግዲህ እንደ እኔ ያለ የጀርመን መድኅን ቅርንጫፍ አባል በጉባዔው ተሳትፈው የተመለሱ አባላቱን ሪፖርት ያዳመጠ የአቶ አሸናፊን ዓይነት መግልጫዎች እንዴት ይመን? ፍርዱን ላንባቢያን እተወዋለሁ። የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቡድን ከላይ በጠቀስኩት መልኩ አንዳንድ ደካማ የቅርንጫፍ አመራር አባል ግለሰቦችን በግል በቅርንጫፉ ስም መግለጫ እንዲያውጡ ከበስተጀርባ ሆኖ ሲገፋፋ ከቆየ በኋላ ኮ/ል ጎሹ ራሳቸው ያንጃው መሪ በመሆን በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ በሚያውጡዋቸው መግለጫዎችና በሚሰጡዋቸው ቃለ መጠይቆች "የሥልት እንጅ የዓላማ ልዩነት በመካከላችን የለም" የሚል ቋንቋ ይዘው በአደባባይ ብቅ አሉ።

## የሥልት ልዩነት

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ፓርቲው ገና ውሳኔ ባልሰጠበት "የትግል ሥልት" ጉዳይ ላይ "በእኛና በወንድሞቻችን መካከል የሥልት እንጂ የዓላማ ልዩነት የለም" ለሚለው አዲሱ ታክቲካቸው ይረዳቸውና ድጋፍ ይሰጣቸው ዘንዳ አስቀድመው "የትግል ሥልት እንድ ውቅቱ ሁኔታ ይለዋወጣል" የሚል መግለጫ አውጥተዋል። እዚህ ላይ ኮሎኔሉ በ6ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ "የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ" በሚል ጽሑፍ በማቅረብ ቀጥሎም ከላይ የጠቀስኩትን መግለጫ በማውጣት ለሁለተኛ ጊዜ የድርጅቱን ደንብ ጣሱ። ከመግለጫው በኋላ በየቃለ መጠይቁና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የስልት እንጂ የዓላማ ልዩነት እንደሌላቸው በመግለጽ ሆን ብለው የድርጅቱን አባላትና አድማጮች ውዥንብር ውስጥ ለመክተትና ድጋፍ ለማግኘት ያልተሳካ ጥረት አደረጉ። በአባላት ዘንድም ትዝብትን አተረፉ። በሌላ በኩል የኮ/ል ጉሹን ሐሳብ የሚቃወሙ አባላት ድርጅቱ በቀረበው የሥልት ለውጥ ላይ ገና ውሳኔ ያልሰጠበት በመሆኑ ተቃውሞአቸውን በአደባባይ ከመግለጽ በመቆጠብ ኮ/ሉ ግን ከደንብ ውጭ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ሽንጣቸውን ገትረው በመቃወምና በማውገዝ ለድርጅታቸው ያላቸውን ታማኝነት ያለማወላወል ገልጸዋል፣ እየገለጹም ናቸው።

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሚያስቡና ለድርጀታቸው የሚቆረቆሩ ቢሆን ኖሮ ሃሳባቸው በድርጅቱ ተቀባይነት እንዲያገኝና የግል እምነታቸው ቀስ በቀስ እያደገና ከግለሰብ አመለካከት ወደ ድርጅታዊ እምነትና ዓላማ

እንዲለወጥ በፖርቲው ውስጥ ሆነው ከመታገል ይልቅ ከውጭ ሆነው መድኅን ውሳኔ ባልሰጠበት ጉዳይ ላይ ልዩነታቸን የሥልት ነው እያሉ ከመስበክ አልፈው የድርጅቱን መሪ የፖለቲካ ሕይወት ለመግደል በመሞከር "እኛ ብዙኃኑ በሰላም ገብተን እንታግል" እንላለን እያሉ ራሳቸውን፣ አቶ ቸሩ ተረፈንና ዶ/ር ሞገስ ገ/ማርያምን እንደብዙኃን፣ የተቀረውን የፓርቲ አመራር አካልና አባላት በሙሉ አናሳ የሚል ስም ሰጥተው "አናሳው የለም በጦርነት እንታግል ይላል" እያሉ ሲሰብኩና በሌላ በኩል ወንድሞቻችን የሚሉዋቸውን በጠረኝነት ሲኮንኑ ስሰማ የኮ/ሉ የፖለቲካ ክስረት አስገርሞኛል። እስኪ እሳቸው የሚነግሩንን እንዳለ እንቀበለውና መልሰን እሳቸውን እንጠይቅ። እንደሚነግሩን ብዙኃን ከሆኑ አነስተኛውን ወገን ለማጋለጥ ይህን ያህል በአደባባይ ላይ ታች እያሉ ድጋፍ ፍለጋ መድከሙንና በአፕሪል 19 አዲስ "የመድኅን ካውንስል" የሚል ድርጅት መፍጠር ለምን አስፈለገ? በእርግጥ ኮ/ሉ ሊያሳምኑን እንደሚፈልጉትስ ልዩነቱ የዓላማ ሰይሆን የሥልት ልዩነት ነውን?

መድኅን በዋሽግተን ዲሲ እ.ኤ.አ  ጁን 17 ቀን 2000 ዓ.ም ሕዝባዊ ስብሰባ ይጠራል። በስብሰባውም ላይ የፓርቲው የቀድሞ ሊቃነመናብርት ኮ/ል ጎሹ ወልዴና ፕ/ር እጅጉ ድምሴ እንዲህም የወቂቱ ሊቀመንበር ፕ/ር ሥዩም ገላዬ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ለስብሰባው ተሳታፊ ንግግርና ገለጻ ያደርጋሉ። ኮ/ል ጎሹ ባደረጉት ንግግር ላይ ማንም ባልጠበቀው ሁኔታ የግል አስተያየቴ ነው በሚል ፓርቲው በጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ "... ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያገኘች አገር በመሆኗ ... እኛ መታገል ያለብን ለተቀረው ኢትዮጵያ ነው" በማለት ንግግራቸውን ይደመድማሉ። ይህ ያልተጠበቀ ንግግር ሁለቱን ሊቃነመብርትና በቦታው የተገኙትን አባላት ክፉኛ ያስደነግጣል። ንግግሩ ወሬ በብርሃን ፍጥነት በሚሰራጭበት በዋሽንግተን ከተማ የተደረገ በመሆኑ ከአንዱ ጆሮ ወደሌላው ፈጥኖ በመዳረስ መድኅን የፖሊሲ ለውጥ እንዳደረገ ተደርጎ ተወራ። ይህ የኮ/ል ንግግር ከአሁን በፊት በኤርትራ ላይ ከነበራቸው ጠንካራ አቋም ጋር ሲተያይ የስማይና የምድር ያህል የተራራቀ ነው። የቀድሞውን ጠንካራ አቋማቸውን ጠንቅቆ ለሚያውቀው የመድኅን አባልም ንግግራቸው አስደንጋጭና አሳዛኝ ዜና ሆነበት። እዚህ ላይ ኮ/ሉ የግል አስተያየታቸውን ባደባባይ ከመግለጻቸው በፊት ቢያንስ ከፓርቲው አመራር ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ኤርትራን በሚመለከት የግል አቋሜ ይህን ይመስላል ብለው የተወያዩበት ቢሆን ኖሮ የፓርቲው አመራርም በእሳቸው ላይ ባላዘነ ነበር። ከዚያ ጊዜ ወዲህ በኮ/ል ጎሹ ወልዴና በተቀሩት በአብዛኛው የፓርቲው የሥ/አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መካከል የነበረው የሥራ ግንኙነት መሃል በዓይን የማይታይ የመስታወት ግድግዳ ተፈጠረ። አቶ ቸሩ ተረፈና ዶ/ር ሞገስ ገ/ማርያም ልክ እንደዛሬው ኮ/ል ጎሹን ደግፈው ከጎናቸው ተሰለፉ።

የኤርትራ ጉዳይ ዝም ተብሎ ለታክቲክና ለፖለቲካ ጠቀሜታ ሲባል ብቻ የሚነሳ ጉዳይ አይደለም። መድኅን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታገል ድርጅት እንድመሆኑ መጠን ኮ/ል ጎሹ በግል እውቅና የሰጥዋትን ኤርትራ በፓርቲው ዓርማ ላይ በሚገኘው የኢትዮጵያ ካርታ ውስጥ አካትቶ ይዟል። ይህ የሆነበት ምክንያት ፓርቲው ከኤርትራ ካርታ ጋር ፍቅር ይዞት ሳይሆን፣ በኤርትራ ውስጥ በኢትዮጵያዊነታቸው የማያምኑ የመኖራቸውን ያህል በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑ የኤርትራ ክ/ሀገር ተውላጆች፣ አፋሮች፣ የሳዎና የኩናማ ብሔረሰቦች በመኖራቸው ከዚሁም በተጨማሪ አሰብ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባሕር በር መሆኗ ምንም የሚያጠያይቅ ባለመሆኑ መድኅን ለዜጎች መብትና ነፃነት እንዲሁም ለብሔራዊ ጥቅምና ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበር የቆመ መሆኑን በፕሮግራሙ ላይ በግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑ ይህን ለሕዝብ የገባውን ቃል ያለበቂ ምክንያት ድንገት ተንስቶ አያጥፍም። በጊዜው ኮ/ል ጎሹ ይህን ተናገሩ ተብሎ ስሰማ ያሳዘነኝ ቢሆንም፣ ከግል አስተያየት ያለፈ ይሆናል ብዬ ግን አልገመትኩም። ዛሬ ግን ኮ/ሉ "እኛ ጦርነት አንፈልግም፣ በሰላማዊ መንገድ ከወያኔ ጋር መታገል እንፈልጋለን" እያሉ በየአደባባዩ ሽንጣቸውን ገትረው ሲሟገቱና አቋማቸውን የማይቀበለውን ሁሉ በጦረኝነት ሲከሱ ስሰማ በዚያ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ በግል አስተያየት ስም በኤርትራ ላይ ያላቸውን አቋም ለሕዝብ ይፋ ያደረጉበትን ንግግር ዛሬ የምመለከተው ከርቀት ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ የተውለበለበ ነጭ ባንዲራ አድርጌ ነው። ስለሆነም እኔ በግሌ ኮ/ል ጎሹ ከመድኅን ጋር ያላቸው ልዩነት የዓላማም የሥልትም ነው ብዬ አምናለሁ፣፣

## የቨርጂኒያ ምሥጢራዊ ስብሰባ፣

የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቡድን አርሊንግተን ከተማ ቨርጂኒያ ውስጥ ያውም የድርጅቱ አባል ያልሆኑ ግለሰቦችን ጨምሮ የምስጢር ስብሰባ በፌብርዋሪ 8 2003 አካሄደ። ይህን በማድረግ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ለሦስተኛ ጊዜ የድርጅቱን ደንብና ሥርዓት ጣሱ። ይህ ምሥጢራዊ ስብሰባ በአፕሪል 19 ቀን 2003 ዓ.ም ሊካሄድ የታሰበውን "ቀጣይ ጉባዔ" ተብየውን ለማካሄድ ይረዳ ዘንድ ስምንት የተለያዩ ኮሚቴዎችን ለማቋቋምና የሥራ ክፍፍል ለማድረግ በኮ/ል ጎሹ የተዘጋጀና በአቶ አበበ ገብረየስ የተፈረመ መግለጫ ፌብርዋሪ 8 ቀን 2003 ዓ.ም ውጥቷል። በተቋቋሙት ስምንት ኮሚቴዎች ውስጥ ኮ/ል ጎሹ በጠቅላላ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢነት፣ በአባላት ምልመላና የጥሪ ደብዳቤዎች አዘጋጅ ን/ኮሚቴ ሰብሳቢና የጉባኤ አዘጋጅ/ጽሑፍ አዘጋጅ ን/ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን የአንድ ኮሚቴና የሁለት ን/ኮሚቴዎች ሰብሳቢ በመሆን ያን ያህል ወርደው በማየቴ በግሌ ደነገጥኩ፣ አዘንኩም። እንዲሁም አቶ ቸሩ ተረፈ በአራት ኮሚቴዎችና ንዑስ ኮሚቴዎች ውስጥ

አባል ሲሆኑ፣ ዶ/ር ሞገስ ገብረማርያም ደግሞ በሦስት ኮሚቴዎችና ንዑስ ኮሚቴዎች ውስጥ የሥራ ድርሻ እንዳላቸው የሥራ ክፍፍሉን የያዘው የስም ዝርዝር ያሳይል። በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ "እኛ ብዙኀን" እያለ ራሱን የሚጠራው ይህ አንጃ ምን ያህል የሰው ድሃ እንደሆነ ያን የኮሚቴ ድልድል የያዘ ዝርዝር የተመለከተ በቀላሉ ይረዳል።

የቨርጂንያው መግለጫ ላይ ስለትጥቅ ትግሉ ሲገልጹ "... ፓርቲው የትጥቅ ትግል ሳያካሂድ እየታገልኩ ነው ብሎ መናገሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትክክለኛ መልዕክት አለመሆኑን በጥሞና በማየቱ ..." የሚል ይገኝበታል። ኮልኔል ጎሹ ወልዴ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ካላቸው ፍላጎት ብቻ በመነሳት መድኅንና አመራሩን በጠረኝነት ይከሳሉ። ስለትጥቅ ትግል ከተነሳ የሚከተለውን ምሳሌ በመጥቀስ ኮ/ል ጎሹን ላስታውሳቸው እወዳለሁ። በመጀመሪያ ደረጃ በመድኅን ውስጥ እንደ እሳቸው የአመራር ጊዜ ስለትጥቅ ትግል የተወራበት ጊዜ የለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ታጠቅ ሰንቅ የሚለውን ሙሉ ንግግራችውን ጳጉሜ 1 ቀን 1985 ዓ.ም ይዞ የወጣው ዕይታ የተባለው ጋዜጣ በወያኔ/ኢህሓዴግ ተመትቶ ከነፃው ፕሬስ የተገለለው እሳቸው የፓርቲው ሊቀመንበር በነበሩበት ጊዜ ባውጁበት ጦርነት ነበር። ነገ ኢትዮጵያ ተመልሰው የዕይታ ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረውን ግለሰብ ቢያገኙት ምን መልሰ እንደሚሰጡት ራሳቸው ይወቁት። መድኅን ያወጣቸው ወታደራዊ መግለጫዎች በሙሉ የወጡት ኮ/ል ጎሹ የፓርቲው ሊቀመንበር በነበሩበት ጊዜ ነው። አቶ መልስ ዜናዊም ቢሆኑ እኛን ኮ/ል ጎሹ ከዋሽንግተን ከተማ ሆኖ በርቀት መቆጣጠሪያ (ሪሞት ኮንትሮል) ይወጋናል ብለን አንፈራም ብለው በመድኅን ላይ ያፌዙበት በኮ/ል ጎሹ ወታደራዊ መግለጫ ምክንያት እንደነበር የዘነጉት መሰለኝ። ከእሳቸው ቀጥሎ የፓርቲውን አመራር የተረከቡት ፕ/ር እጅጉ ደምሴና  የወቅቱ ሊቀመንበር ፕ/ር ሥዩም ገላዬ የመሩትና እየመሩት ያለው መድኅን ስለትጥቅ ትግል ያወጣው አንድም ወታደራዊ መግለጫ የለም፤፣ ኮ/ል ጎሹ ታዲያ የትኛውን መድኅንን ነው የሚከሱት? ጠረኛውስ ማነው? ሌላው ሁሉም እንደሚገነዘብው መድኅንን ጨምሮ የኢትዮጵያ እውነተኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች ምን ዓይነት የትግል ስልት መከተል እንዳለባቸው መወሰን ያለበት በአብዛኛው የአባላት ውሳኔ እንጂ በግለሰብ ፍላጎት እንዳልሆነ አያጠያይቅም። ካልሆነ ግን ከወያኔ አይሻሉም። ሌላው የሰላሙን መንገድ ሁሉ በመዝጋትና ምርጫ በማሳጣት ሌላ የትግል ስልት እንዲከተሉ የሚያስገድዳቸው በመሣሪያ ኃይል ሥልጣን ጨብጦ የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃነትና መብት ረግጦ እየገዛ የሚገኘው የመለስ ዜናዊ መንግስት ሰላምን የመፈለግና ያለመፈለግ ጉዳይ ነው።

የቨርጅንያው ምሥጢራዊ ስብሰባ ከድርጅቱ አመራርና አባላት እውቅና ውጪ የተካሄደ ሕገወጥ ተግባር በመሆኑ የፓርቲው አመራር በኮ/ል ጎሹ ወልዴ ላይ የካቲት 19 ቀን 1995 ዓ.ም የወሰደውን አስተዳደርዊ እርምጃ እንደማንኛውም አባል በመደገፍ ተገቢና ትክክለኛ ነው ብዬ አምናለሁ፤፣ እንኳን እንደ መድኅን ያለ ታግሎ ለማታግል የቆመ የፖለቲካ ድርጅት ይቅርና በማሕበራዊ ሕይወት እንቅስቃሴዎቻችን ውስጥ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱት የሠፈር ውስጥ እቁብና እድሮች እንኳን የተቋቋሙበትን ዓላምና እቅድ በተግባር ለማዋል ይረዳቸው ዘንድ የመተዳደሪያ ደንብ ቀርጸው እንደሚንቀሳቀሱ ትንሿ ልጄ ሳትቀር ጠንቅቃ ታውቃለች። በመሆኑም የድርጅቱን ደንብ ማክበር የማንኛውም አባል የመጀመሪያ ግዴታ ነው። የመተዳደሪያ ደንቡ በሁሉም አባላት ዘንድ እኩል መከበር ይኖርበታል። እንደነ ዶ/ር ፀሐይ ዓለማየሁ፣ ዶ/ር ፍስሐጽዮን መንግሥቱ የመሳሰሉት አንጋፋ የመድኅን መስራችና የፓርቲው ክፍተኛ የአመራር አባላት ከፓርቲው በኮ/ል ጎሹ አመራር የተሰናበቱት የድርጅቱን ድንብ በመጣስ በመንቀሳቀሳቸው እንጂ ሌላ የፈጸሙት ወንጀል ኖሮ አይደለም። የእነዚህን ሁለት የመድኅን መስራቾች ከፓርቲው መሰናበት በወቅቱ የደገፍኩ ቢሆንም ከፓርቲው የተሰናበቱ መሆናቸውን አስመልክቶ በጁን 12ቀን 1994 ዓ.ም በወጣው መግለጫ ውስጥ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ዶ/ር ፀሐይ ዓለማየሁን በሚመለከት በቁጥር 9 ላይ "... ይህ መጥፎ አድርጎ በማንኛውም አገርና ደሞክራሲያዊ መንግስት ሥርዓት ውስጥ ለከፍተኛ ቅጣት (ሞት ጭምር) የሚያበቃ የአገር መክዳት ወንጀል ነው።" የሚለውን ነጥብ በጊዜውም  ሆነ ዛሬ ፈጽሞ ሊገባኝ አልቻለም። እዚህ ላይ ምን ማለት እንድፈለጉ ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ ውጭ የገባው ሰው ያለ አይመስለኝም። ለእኔ ግን ግልጽ የሆነልኝ ነገር ቢኖር ኮ/ል ጎሹ ምን ያህል ስሜታዊና እልኸኛ ሰው እንደሆኑ ነው።

## "የመድኅን 6ኛው ቀጣይ ጉባኤ"

የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቡድን ገና መድኅን ባልወሰነበት ጉዳይ ላይ የተወሰነበት ይመስል በየአደባባዩ በእኛና በወንድሞቻችን መካከል ያለው ልዩነት "የዓላማ ሳይሆን የስልት ብቻ ነው" በማለት የሚሰብክበትን የሰላም ፖለቲካ ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት ይረዳው ዘንድ "የመድኅን 6ኛው ቀጣይ ጉባኤ“ የሚባል ቲያትር እንደሚያካሂድ በይፋ አሳወቀ። የተሰጠው ምክንያትም ያለፈው የመድኅን 6ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ፓርቲውን የሚመራው ከፍተኛ የአመራር አካል አልመረጠም የሚል ስንካላ ምክንያት ነው። የመድኅን ጠቅላላ ጉባኤ የአመራር አካሉን ሲመርጥ እንደ ባህል አድርጎ የያዘው የአመራረጥ ስልት አለው። የኦክቶበር 19 ቀን 2002 ዓ.ም ጉባኤ የምርጫ ሂደትም ይህንኑ የተለመደ አሠራር የተከተለ ነበር። ይኸውም አገልግሎቱን ጨርሶ የሚወጣው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ፓርቲውን ለመምራት ይመጥናሉ ብሎ ያመነባቸውን እጩዎች ከነተጠባባቂዎቻቸው ለጉባኤው ያቀርባል። ጉባኤውም ከቀረቡት

እጩዎች መካከል ፓርቲውን ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የሚመሩ አባላትን ይመርጣል። የኦክቶበር 19 ቀን 2002 ዓ.ም ምርጫም በዚህ መልኩ ነው የተካሄደው። በዚህ መሠረት ፕ/ር ሥዩም ገላዬ በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ በሊቀመንበርነት በመመረጣቸው የጉባኤው ተሳታፊ የተሰማውን ደስታ  ኮ/ል ጎሹን ጨምሮ ከመቀመጫው ተነስቶ እያጨበጨበ ደስታውን ገልጿል። በአዲሱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ ኮሎኔል ጎሹ ወልዴም በአባልነት ይመረጣሉ። በዚህን ጊዜ ኮ/ሉ ከተቀመጡበት ይነሱና ከአሁን በኋላ በሥ/አ/ኮሚቴ አባልነት መቀጠል የማይፈልጉ መሆናቸውን ገልጸው፣ ነገር ግን ከአንድ የሥ/አ/ኮሚቴ አባል ባላነሰ ሁኔታ በንቃት እንደሚሳተፉና የሚሰጣቸውን ሥራ ሁሉ እንድሚያከናውኑና ከትግሉ ወደኋላ እንደማይሉ ቃል ይገባሉ። ቀጥሎም አቶ ቸሩ ተረፈ ተነስተው በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባልነት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በፓርቲው ውስጥ በአባልነት መቀጠል እንደማይፈልጉና የጤንነታቸውን ጉዳይ በማንሳት በተጨማሪ አንዳንድ አገር ቤት ውስጥ መሥራት የሚፈልጉት ነገር እንዳላቸው ገልጸው፤ ሆኖም ግን መድኅን ምንጊዜም ቢሆን ከአእምሯቸው እንድማይጠፋ በመግለጽ አንድ የቀድሞ የኢሕአፓ አባል ስለ ኢሕአፓ ተናገረ የተባለውን የእንግሊዝኛ ጥቅስ በማንሳት ራሳቸውን ከመድኅን ማግለላቸውን በጉባኤው ፊት አሳወቁ። ዶ/ር ሞገስ ገ/ማርያምም በድርጅቱ ውስጥ መቀጠል እንደማይፈልጉ ገልጸው ስብሰባው ሳያልቅ አዳራሹን ጥለው ወጡ። እንግዲህ በጉባኤው ዕለት የቀረበው የትግል ስልት በሚፈልጉት መልክ በዕለቱ ውሳኔ ስለአላገኘ ብቻ ኮ/ል ጎሹ፣ አቶ ቸሩና ዶ/ር ሞገስ ከላይ የጠቅስኩትን እርምጃ ወስደዋል። በዚህ ዓይነት መንገድ በመድኅን 6ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ራሳቸውን ከፓለቲካ አመራርና ከአባልነት ያገለሉ ግለሰቦች ጉባኤው በተካሄደ ጥቂት ውራት ውስጥ የመድኅን 6ኛ ቀጣይ ጉባኤ የሚሉትን ቲያትር ለመጥራት ሲሯሯጡ ማየት ከሚሰጠው መልስ ይልቅ በእያንዳንዱ ታዛቢ አእምሮ ውስጥ የሚመላለሱ ጥያቄዎች ይበልጣሉ። ስለምርጫ ከተንሳ መድኅን 4ኙውን ጉባኤ ባካሄደበት ወቅት ገና የስብሰባው ሂደት ሳይጠናቀቅ ኮ/ል ጎሹ በመሐል አድራሹን ለቅቀው ይወጡና በሄዱበት ይቀራሉ። በሁኔታው ግራ የተጋቡ የጉባኤ ተሳታፊዎች በእረፍት ሰዓት ኮ/ሉ አጠገብ ተቀምጠው የነበሩትን አባል "ምንው ኮሎኔል ጉባዔው ሳያልቅ ጥለው ሄዱ? አሟቸው ይሆን? ብለው ሲጠይቁ ተጠያቂው ውስጥ አዋቂ የለም ፓስተር እገሌ ወደ ሀገር ቤት ስለሚሄድ እሱን ለመሸኘት ነው ኤርፖርት የሄዱት በማለት ይመልሱላቸዋል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን እርሳቸው ስብሰባ አቋርጠው ቢሄዱም ጉባኤው ግን በሌሉበት በፓርቲው ሥራ አስፈጻሚና በምክር ቤት ኮሚቴ አባልነት በወቅቱ ይመርጣቸዋል። እርሳቸውም በሌለሁበት ነው የተመረጥኩት ብለው ምርጫውን አልተቃወሙም። ዛሬ ግን ሁሉም ነገር ተገለባበጠና ምርጫው በመተዳደሪያ ድንቡ መሠረት አልተካሄም ተባለና 6ኛው ቀጣይ ጉባኤ መካሄድ አለበት በማለት ሁኔታውን በደንብ ያልተከታተሉ ገራገር አባላትን አሳስተው በአንጃ መሪነት ራሳቸውን ሹመው አደባባይ ብቅ አሉ።

## አፍንጫ ረጅሙ ፕሮፓጋንዳ

የመድኅን ድምፅ የሬዲዮ ስርጭት የኢትዮጵያን ሕዝብ የማወቅ መብት ለማስከበር፣ የወያኔ/ኢሕአዴግ አምባገነን አገዛዝ በአገርና በሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን በደል ለማጋልጥና ድምጽ የተነፈገውን እውነተኛ የተቃዋሚ ኃይል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚገናኝበትን መድረክ ለመፍጠር ታስቦ የተጀመረ የሬዲዮ ስረጭት ነው። ይህ ዝግጅት የሚተዳደረው ሰባት አባላትን በያዘ ቦርድ ሲሆን ከነዚህም አባላት መካከል አቶ ማሞ ይሁኔና አቶ ጥላሁን ሲሳይ መድኅንን ከድተው የእነ ኮ/ል ጎሹን አንጃ በመቀላል የመድኅን ድምጽ የተቋቋመበትን ዓላማ በሳተ መልኩ የአንጃው አፍ በመሆን በፓርቲው አመራርና አባላት ላይ ከፍተኛ የማጥላላት ዘመቻ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ መድኅን ደሞክራሲያዊ ፓርቲ የአመራር አካል ፈጥኖ በወሰደው እርምጃ የመድኅን ድምጽ ሬዲዮ ዝግጅት የቆምለትን ዓላማ እንዳይስትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሰጠውን አገልግሎት እንዳያቋርጥ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የአቶ ማሞ ይሁኔን ውክልና በማንሳትና ሌላ ሰው በመተካት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሬዲዮ አገልግሎቱ እንዲቀጥልና ለኢንተርኔት አድማጮችም በ www.Medhininfo.com ወይም በ www.medhin.org ድህረ ገጾችን በመጠቀም የራዲዮኑን ፕሮግራም በማስተላለፍ የተፈጠረውን ክፍተት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመሙላት ተችሏል። ሆኖም ግን የአቶ ማሞ ይሁኔ የኢንተርኔት ሬዲዮ ፕሮግራም (የግል ማለት ይቻላል) ኮ/ል ጎሹ ራሳቸው ሊያዙበት እንደማይችሉና ምንም ቅንጅት እንደሌው ከሚያስተላልፈው ፕሮግራም መረዳት ይቻላል። ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ ለመጥቀስ ያህል ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ለአንድ የሬዲዮ ፕሮግራም የሰጡትን ቃለ ምልልስ በአፕሪል 13 በዚሁ በእነ አቶ ማሞ የኢንተርኔት ሬዲዮ ፕሮግራም ይተላለፋል። ጠያቂው ኮ/ል ጎሹን የአፕሪል 19 ጉባኤ ዓላማው ምንድንነው ብሎ ይጠይቃቸዋል። ኮ/ል ጎሹ ሲመልሱ "... አዲሱ የትግል ስልት ላይ ለመወሰን ... ስልቱ የሚወሰነው  በጉባኤው ነው። ... ጉባኤው የሚያሳልፈው ውሳኔ የፓርቲው ፖሊሲ ይሆናል።" ብለው ይመልሳሉ። የአቶ ማሞ ይሁኔ የኢንተርኔት ሬዲዮ ደግሞ ኮ/ል ጎሹን ቀድሞ በፌብርዋሪ 27 እና በማርች 6 ባስተላለፈው ፕሮግራም "መድኅን አዲስ ፖሊሲ ቀየሰ" ብሎ ዜናውን አስተላለፈ። ይህም አልበቃ ብሎ በማርች 23 ባሰራጨው ፕሮግራሙ "መድኅን ውስጥ ስለተፈጠረው መከፋፈል ኢትዮጵያውያንን ለማሳወቅ ተብሎ በዋሽግተን ከተማ በተካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የድርጅቱ መሥራችና መድኅንን ለ4 ዓመታት ተኩል የመሩት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ለተሰብሳቢው ያደረጉትን ንግግር ከዜናው በኋላ እናሰማለን ተብሎ ኮ/ሉ እ.እ.አ ጁን 17 ቀን 2000 ዓ.ም በዋሽግተን ዲሲ መድኅን በጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ካደረጉት ንግግር ውስጥ የተወሰነውን ወስዶ

በማስተላለፍ በኮሎኔል ጎሹ ላይ አፌዥባቸዋል። የዚህ ዓይነቱ እጅና እግር የሌለው የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ብዙ አባላትን ገና ከጅምሩ የነበራቸውን ጥርጣሬ ያረጋገጠላቸው በመሆኑ የኮ/ል ጎሹ ቡድንን ማንነት የበለጠ ያጋለጠ ነው። አቶ ማሞ ይሁኔ ፕሮፓጋንዳቸው ተመልሶ ራሳቸውን ስለመታቸው፣ የማርች 23 ፕሮግራማቸውን ከኢንተርኔት ሠርዘውታል። እኔ በግሌ ይህ ሁሉ ቲያትር የመድኅን ታሪክ አንድ አካል በመሆኑ ቀድቼ አስቀምጬዋለሁ።

## አፕሪል 19

በግል የኢንተርኔት ሬዲዮ ራሱን እኛ ብዙኀን የመድኅን ቅርንጫፎች፣ እኛ አብዛኛው የሥ/አ/ኮሚቴ አባላት፣ በአገር ውስጥና በውጭ ከፍተኛ ድጋፍ እያገኘን ነው በማለት የሚያስወራው የኮ/ል ጎሹ ቡድን በመላው ዓለም የሚገኙ የመድኅን ቅርንጫፎች ለጉባኤው መሳካት የሚያደርጉትን ዝግጅት ማጠናቀቃቸውንና በጉባኤው ላይ የሚሳተፉ አባላት ከመላው ዓለም ወደ ዋሽግተን ዲሲ ከየአቅጣጫው እየገቡ እንደሆነ የተወራለት ጉባዔ ቀኑ ደርሶ አፕሪል 19 ከአውሮፓ አምስት ግለሰቦች ያውም ትራንስፖርቱ ተችሎላቸው ሲገኙ የተቀሩት ከዚያው ከሰሜን አሜሪካ ከየስቴቱ ተለቃቅመው የተገኙት ሃያ የማይሞሉ ነበሩ። ይህ ስብስብ ኮ/ል ጎሹን ራሱን "የመድኅን ካውንስል" ብሎ የሚጠራው አንጃ ፕሬዚዳንት አድርጎ በመምረጥ ድርጅታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ትግል እንደሚያካሂድ ይፋ አድርጓል። አንጃው በመድኅን የመተዳደሪያ ድንብ ውስጥ ፈጽሞ የሌለ መዋቅር በመፍጠር የድርጅቱን መሪ “ፕሬዚዳንት“ የሚል መጠሪያ በመስጠት የራሱን ድርጅት ፈጥሯል። ኮሎኔል ጎሹና ግብረአበሮቻቸው ከመድኅን የተሰናበቱ መሆናቸውንና አንጃ ፈጥረው በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት እንዳቀዱ የመድኅን ድምጽ ሬዲዮ በውቅቱ ያስተላለፈው የመድኅን መግለጫና ባገር ውስጥ የሚገኙ የነፃው ፕሬስ ውጤቶች ለሕዝብ ጆሮና ዓይን ማብቃታቸው ይታወቃል። ከአፕሪል 19 በኋላ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት እድሜ ለኮ/ል ጎሹ ወልዴ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ብዛት በአንድ ቁጥር ጨመረ፣ ትግሉ ግን አንድ እርምጃ ወደ ኋላ አፈገፈገ፡፤ በዚያው መጠንም የአቶ መለስ አገዛዝ እድሜ ተጠናክሮ ተራዘመ። አያሳዝንም?

## ምን ትምህርት አገኘን?

መቼም ቢሆን መድኅን ውስጥ በተፈጠረው ሁኔታ የሚደሰት አባልም ሆነ ደገፊ ይኖራል ብዬ አልገምትም። ለወያኔ/ኢሕአዴግና ለደጋፊዎቹ ግን ከዚህ የበለጠ አስደሳች ዜና እንደሌለ አንድና ሁለት የለውም። በሌላ በኩል ደግሞ ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይሎችን ሕብረት ማየት ለሚፈልገው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመድኅን ውስጥ የተፈጠረው መከፋፈል የመርዶ ያህል እንደሚከብድ ግልጽ ነው። የአንድ ድርጅት አመራር ጥንካሬ የሚለካው በፓርቲው ውስጥ ችግር ሲፈጠር የሚወስደው የመፍትሄ እርምጃ በአባላቱ ዘንድ ተቀባይነትን ሲያገኝ ነው። ጀርመኖች አንድ የምወድላቸው አባባል አላቸው። ይኸውም "አንድ ችግር ራሱ መፈትሄውንም አብሮ ይዞ ይመጣል" ይላሉ። እንደ መድኅን ያሉ በሕጋዊ መንገድ አገር ውስጥ ገብተው እንዳይንቀሳቀሱ የታገዱ የፖለቲካ ድርጅቶች ትግል የሚያካሂዱት ከአገር ውጭ በመሆኑ ብዙውን ሥራ የሚያከናውኑትም በእምነት ላይ ተመስርተው ነው። ስለሆነም የድርጅት ንብረት በግለሰብ ስም ማስቀመጥና ማስመዝገብ አዲስ ነገር አይደለም። በአንድ ወቅት ላይ ግለሰቦች ከድርጅት የሚያፈንግጡበት ሁኔታ ሲፈጠርም በስማቸው ያለውን ንብረት እንደያዙ ከድርጅቱ ራሳቸውን ያገልላሉ። መድኅን ተመሳሳይ ሁኔታ ብዙውን ጊዜ ያጋጠመው ቢሆንም በግለሰብ ስም ተመዝግቦ የነበረውን የድርጅቱን Domain የያዘው ግለሰብ ፈጥኖ አንጃዉን በመቀላቀሉ መድኅን ፈጥኖ በሌላ Domain በማግስቱ ሊተካው በመቻሉ ግለሰቡን ትዝብት ላይ ሲጥል አንጃው ደግሞ የፓርቲው አመራር የወሰደው ፈጣን ርምጃ ያልጠበቀው ስለነበር ድንጋጤ ላይ ጥሎታል። የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ከእንዲህ አይነቱ አሠራር ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉም በዚህ አጋጣሚ ማሳሰብ እወዳለሁ። ሌላው ወደፊት አንጃዎች በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ እየተፈጠሩ ትግሉን እንዳያዳክሙ ተቃዋሚ ኃይሎች በጋራ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ከወዲሁ ሊያስቡበት ይገባል። አለዚያ አንጃዎች በየድርጅቱ እየተፈለፈሉ የሕብረቱን ጥንካሬ የሚፈታተኑ ይሆናሉ የሚል ስጋት አለኝ። ስለዚህ ጥያቄው ምን መደረግ አለበት የሚል ይሆናል? መልሱ በጣም ቀላል ነው። የተቃዋሚ ኃይሎች ህብረት እስከዛሬ ድረስ ይከተል ከነበረው አሰራር አንድ እርምጃ ወደፊት በመራመድ የአባል ድርጅቶችን ድክመትና ጥንካሬ እንደ ራስ ጥንካሬና ድክመት በማየት ከደንብና ከሥርዓት ውጭ በአባል ድርጅቶች ውስጥ የሚፈጠሩ አንጃዎች አባል ድርጅቶችን የሚያዳክሙና በሕብረቱ ፖለቲካ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ በማስግባት እንዲህ ዓይነቱን አንጃ በአደባባይ በማውገዝና እውቅና በመንፈግ ከትግል ሜዳው የማግለል ልምድና ባሕል መለመድ አለበት የሚል እምነት አለኝ። ይህም መሆን ያለበት ያለምክንያት አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር የማንም ተስፈንጣሪ ቡድን የፕሮፓጋንዳ መሣሪያና ድብቅ አጀንዳ ማስፈጸሚያ መሆን አይኖርበትም። በዚህ መልኩ አለአግባብ በጥቂት ሰዎች ፍላጎት በድርጅት ውስጥ የሚፈጠርን አንጃ በአደባባይ የማግለሉ ባሕል ትምህርት ሰጪ ሊሆን ስለሚችል ሙሉ በሙሉ የአንጃዎችን

መፈጠር ያስቀራል የሚል እምነት ባይኖረኝም የአንጃዎችን መፈጠር ሊቀንስና አንጃው የተፈጠረበትን ድርጅት የትግል ሞራል እንዳይጎዳ ሊከላከል ይችላል ብዬ አምናለሁ።

ከዚህም በተጨማሪ በያንዳንዱ አባል ድርጅት ውስጥ አባላት የፓርቲው ውስጠ ዲሞክራሲ እንዲያድግና እንዲጎለብት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይገባል፡፤ በድርጅት ውስጥ ምንም ዓይነት ልንወያይበት የማንፈልገውና የምንፈራው አጅንዳ መኖር የለበትም። በሁሉም ጉዳዮች ላይ በግልጽ መወያየት መቻሉ በራሱ በድርጅት ውስጥ ሊፈጠር የሚችልን አንጃ እድል ያሳጣል።መድኅን ውስጠ ዲሞክራሲ የአሠራር ባሕል ያለውና የሥልጣን መፈራረቅን እንደ ባሕል አድርጎ በመያዝ ከብዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች በተለየ መልኩ ፓርቲው ሊቃነመናብርትን መቀያየር መቻሉ በራሱ የድርጅቱ ውስጠ ዲሞክራሲ መግለጫ አንዱ ገጽታ ነው። ከላይ እንደገለጽኩት ውስጠ ዲሞክራሲያዊ አሠራር ብቻውን መድኅንን ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ አንጃ ባያድነውም አንጃው ብዙ ደጋፊ እንዳያገኝ እንዳደረገው ግን ለማየት ተችሏል።

## ማጠቃለያ

ባንድ ድርጅት ውስጥ የተለያዩ የአመለካከት ልዩነቶች መኖራቸው ጤነኛና ለፓርቲው ጥንካሬ የሚኖራቸውን ጠቀሜታ የሚያጣ ፓለቲከኛ ያለ አይመስለኝም። በመሆኑም እንኳን በፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ቀርቶ በተለያዩ ትናንሽ ማኅበራት ውስጥ እንኳን ሳይቀር የአመለካከት ልዩነትን ምክንያት አድርጎ የሚከሰት ያሰራር ችግር ያለና የነበረ በመሆኑ ለማንም ቢሆን እንግዳ ነገር አይደለም። የአመለካከት ልዩነት ከሰው ልጅ ጋር አብሮ የተፈጠረ፣ ያለና ወደፊትም የሚኖር ሰብዓዊ ባሕርያችን በመሆኑ በማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ሊከሰት የሚችል ነው። በመድኅን ውስጥ የተፈጠረውን ሁኔታ የምመለከተው ከዚህ አኳያ ነው። ሆኖም ግን ሊገባኝ ያልቻለው እንደ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ያለ በእውቀትና በእድሜ የበሰለ ፖለቲከኛ ልዩነትም ካለ ቢቻል ገንቢ በሆነ መልኩ ልዩነትን አጥብቦ የግል አመለካከታቸውና እምነታቸው አድጎ የፓርቲው አመለካከትና እምነት እንዲሆን መድኅን ውስጥ ሆኖ መታገልና ሃሳባቸው ድጋፍ እንዲያገኝ መጣር፣ ተቀባይነት ካጣ ደግሞ እራስን ለብዙኀን ውሳኔ ማስገዛት፣ ካልሆነም ፓርቲውን ለቆ በመውጣት ተመሳሳይ ዓላማ የሚያራምድ ድርጅት ጋር መቀላቀል፣ ይህም የማይቻል ከሆነ በአፕሪል 19 ቀን 2003 ዓ.ም እንድተደረገው አዲስ "የመድኅን ካውንስል" የተባለ የራስን ድርጅት ፈጥሮ የድርጅቱም ፕሬዚዳንት ሆኖ መታገል እየተቻለ ገና ሐሳቡ ቀርቦ አባላት ተወያይተውበት እንኳን ሳይጨርሱ ፈጥኖ "የትግል ሥልት እንደወቅቱ ሁኔታ ይለውጣል" የሚል መግለጫ በማንአለብኝነት ማውጣት፣ ራስን ሰላም ወዳድና ሌላውን ጦርነት ናፋቂ፣ በየተገኘው አጋጣሚ እኛ አገሪቷ መሬቱ፣ ሕዝቧ ናፍቆናል በማለት ሌላውን አገርና ወገኑን የማይናፍቅ በማስመሰል በፓርቲው አመራርና በአባላቱ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ አዘል ፕሮፓጋንዳ ማካሄድና ወያኔ ሞክሮት ያልተሳካለትን አሉቧልታ በፓርቲው ላይ መንዛት ለማንም ሊገባው ያልቻለ እንቆቅልሽ ሆኗል። በመሆኑም ኮ/ል ጎሹ ገና በሕይወት እያሉ በመድኅን ታሪክ ውስጥ በአዎንታዊና በአሉታዊ መልኩ ሲዘከር የሚኖር ታሪክ ማስመዝገብ ችለዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ መታገል የማይፈልግ ድርጅት ሊኖር አይችልም።የፖለቲካ ድርጅትም የመጨረሻ ግቡ የፖለቲካ ሥልጣን እንደመሆኑ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ሳይኮን የፖርቲን ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል ማንም የፖለቲካ ሀሁ የቆጠረ ያውቀዋል። ሆኖም ግን ጥያቄው አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ እውነተኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው እንዲታገሉ ፍላጎቱ አለውን? በአገር ውስጥ የሚገኙ አራት እውነተኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የሁላችንንም አድናቆትን ከበሬታን ያተረፉ መሆኑ ጥያቄ ውስጥ  ሳይገባ በነፃ የመንቀሳቀስ መብታቸው ምን ይመስላል ወይም እስከምን ድረስ ነው? ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በሰላማዊ መንገድ ገብተን መታገል እንፈልጋለን ሲሉ ምን ያደረጉት ቅድመ ዝግጅት ኖሮ ነውን? ትላንት በወያኔ አምባገነን አስከፊ አገዛዝ ላይ ሲያነሱዋቸው የነበሩዋቸው ጥያቄዎች ስንቶቹ መልስ አግኝተዋል? የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውና የሚመኘው ዓይነት የተቃዋሚዎች ሕብረት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ አለ ወይ? በተቃዋሚዎችና በሙያ ማኅበራት መካከል መኖር የሚገባው የትግል መደጋገፍና ህብረት አለን? ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝባዊ አመጽ ለማስነሳት ጅምሩ አለ ወይ? ... የመሳሰሉትን ሌሎች ብዙ ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል። ወይስ ኮ/ል ጎሹ እንድሚሉት ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ የዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሁኔታና የኃይል አሰላለፍ የፈጥረው ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ይዘትና ዝንባሌ በተለይም ከሴፕቴምበር 11 ወዲህ በዓለማችን ላይ የተፈጠረው ሁኔታ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች አገር ቤት ገብተው በሕግ ታቀፉው ወይም በግልጽ ቋንቋ ለወያኔ እጅ ሰጥቶ ከመታገል ውጪ ሌላ አማራጭ የላቸውም ነው የሚሉን? በእርግጥ የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ድጋፍ አስፈላጊና በአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ላይ የሚኖረው ተጽኖ ቀላል አይደለም። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች የእምነታቸው መሠረት ግን መሆን ያለበት ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ናቸው። ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይሎች ሕብረት ተፈጥሮ ከሙያ ማሕበራት ጋር እጅና ጓንት ሆኖ በመሥራት ሕዝቡን ከጎን በማሰለፍ በወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ላይ ሕዝቡን ማስነሳት   ሲጀመር የዓለም አቀፍ  ሕብረተሰብ ያለማንም ጥሪ ፈጥኖ ድጋፉን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚሰጥና ወያኔም ራሱን ለጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት ከማስገዛት

ውጭ አማራጭ እንደማይኖረው በብዙ የአፍሪካ አገሮች የታየና በደርግ ውድቀት መጨረሻ ሰዓት ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ በተግባር የታየ እውነታ እንደነበር አይዘነጋም።

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ያቀረቡት ሐሳብ በመድኅን 6ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ቀርቦ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሚጠራ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉባኤው ያሳለፈውን ውሳኔ በመጣስ የፓርቲውን ድንብ በመተላለፍ ተንቀሳቅሰው አንጃ መፍጠራቸው የሚያሳዝን ነው። እንደ እኔ ድርጅቱ በተመሠረተ ማግሥት ፓርቲውን የተቀላቀለ አባል ሰውነቱ ለመድኅን ስድስተኛ የስሜት ሕዋስ ይፈጥራል። እኔ ኮ/ል ጎሹ ባቀረቡት ሐሳብ ላይ ለመወያየት ትናንትም ዛሬም ይሁን ነገ ችግር የለብኝም። ሆኖም ግን የኮ/ል ጎሹ ቡድን ራሱን ለውይይት ማስገዛት አቅቶት ከፓርቲው ደንብ ውጭ ሲንቀሳቀስ ሳይ ሕለናዬና ስድስተኛው የስሜት ሕዋሴ ኮ/ል ጎሹ ወልዴና ግብረአብሮቻቸውን እንድወቅስና እንዳወግዝ ያስገድዱኛል። ስለፓርቲ ምሥረታ ሳነሳ አንድ ነገር ትዝ አለኝ። መድኅን ተመሥርቶ ኮ/ል ጎሹ የፓርቲው ሊቀመንበር በነበሩበት ጊዜ አቶ ቸሩ ተረፈ ኮሎኔሉን ለሎሳንጀለስ ቅርንጫፍ ሲያስተዋውቁ፣ "የወያኔ/ኢሕአዴግን አገዛዝና የጎሳ ፖለቲካውን ከደገፍክ ሥልጣን እንሰጥሃለን ተብሎ እምቢ ያለው ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ማለት ይህ ሰው ነው" በማለት አስተዋውቀዋቸ ነበር። ወደፊት ደግሞ ሌሎች ምን ብለው እንደሚያስተዋውቁዋቸው እድሜና ጤናውን ይስጠን እንጅ እንሰማለን። አንድ ፖለቲከኛ ያለው የመጨረሻ ምኞትና ሕልም ቢኖር የሕዝብ አመኔታን ማግኘት ነው። የሕዝብ አመኔታ ደግሞ በተግባር እንጂ በባዶ ወሬ ብቻ የሚገኝ አይደለም። ክቡር ፕሬዚዳንት የተናገሩትን ሁሉ ያልሰማ የለም። የቀረው ተግባር ብቻ ነው። የቀድሞ የትግል አጋርዎ እንደመሆኔ መጠን መንገዱን ጨርቅ ያድርግልዎ ዘንድ ከልቤ እየተመኘሁ ጽሑፌን በዚሁ አበቃልሁ።